# የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት

☏ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251 116– 55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa, Ethiopia e-mail:-allethiopiaunityparty@gmail.com

# ALL ETHIOPIA UNITY PARTY


ቁጥር
Ref No. ____________
ቀን
Date 07/12/2004

ለኢሳት የሚዲያ ተቋም

ጉዳዩ: ኢሳት በመኢአድ ላይ የሚያስተላልፈውን የሃሰት ፕሮጋንዳና የቅስቀሳ ሥርጭት እንዲያቆም ስለመጠየቅ

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በኢትዮጵያ ውስጥ የመጻፍ፣ የመናገር፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማካሄድ፣ የሥራ ማቆም አድማ የማድረግ በህይወት የመኖር፣ ሰባዊ ክብር የመጠበቅ፣ የመስራት፣ የመመገብ እና ሌሎችም ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችም እንዲከበሩ በጽናት ይታገላል፡፡ መኢአድ ኢትዮጵያውያን ከወያኔ አህአዴግ የአፈናና የረገጣ አገዛዝ ተላቀው ህዝብ በወደደውና በመረጠው መሪ የሚተዳደርበት ሥርዓት እንዲመጣ በቁርጠኝነት የሚታገል ሃቀኛ ድርጅት መሆኑ ይታወቃል፡፡ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ሰላማዊ የትግል መንገድ መርጦ በሚያካሄደው ቁርጠኛ ትግል መሪዎቹና አባሎቹ ግድያ፣ እስራት፣ ድብደባ እና ሌሎችም ሰቆቃዎች እየተፈጸሙባቸው ይገኛል፡፡

የመኢአድ አባላት ላለፉት ሃያ ዓመታት ክቡር ህይወታቸውን በመገበር ጭምር መስዋዕትነት በመክፈል አምባገነኑን የወያኔን ህገ ወጥ ቡድን ፊት ለፊት ተጋፍጠው ተጨባጭ ውጤት ያስመዘገቡና አሁንም በማስመዝገብ የሚገኙ ናቸው፡፡ መኢአድ በመላው ኢትዮጵያ ባሉ ክልሎች ውስጥ መዋቅሩን ዘርግቶ በስፋት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ህብረ ብሔራዊ ፓርቲ መሆኑ ይታወቃል፡፡

መኢአድ እዚህ ደረጃ ለመድረስ ብዙ ዋጋ ከፍሏል፡፡ ፓርቲያችን በታላቁ የነፃነት አርበኛ በክቡር ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስና በየደረጃው በነበሩ አመራሮችና አባላት ደምና አጥንት የተገነባ በመሆኑ ለወያኔ ፍርፋሪ በሚደለሉ አድርባዮች የማይንበረከክና ከጉዞውም የማይናወጥ መሆኑን ደጋግሞ አስመስክሯል፡፡

ለህዝብ መብት መከበር በቆመው መኢአድ ላይ ኢሳት የሚዲያ ተቋም በተለያዩ ጊዜያት እያካሄደ ያለው አፍራሽ ቅስቀሳ እጅግ ያሳዘነን መሆኑን ልንገልጽላችሁ እንወዳለን፡፡

ከአፍራሽ ቅስቀሳዎቹ ውስጥም፣ ቀድሞ የመኢአድ አባል የነበሩት አቶ ያሬድ ግርማ በፈጸሙት የዲስፕሊን ጥሰት ምክንያት በመኢአድ ማዕከላዊ ኮሚቴ ውሳኔ ከፓርቲው መሰናበታቸው ይታወቃል፤ ነገር ግን የኢሳት ማሰራጫ ጣቢያ አቶ ያሬድ ግርማ ልክ አሁንም የመኢአድ አባል እንደሆኑ አስመስሎ በመጋበዝ ቃለ መጠይቅ ማካሄዱና በቃለ መጠይቁም በመኢአድ ላይ አፍራሽ የሆኑ የሃሰት መረጃዎች መሠራጨታቸው አንዱ ነው።

በሌላ ወቅትም ልክ እንደ አቶ ያሬድ ግርማ ሁሉ በዲስፕሊን ጉድለት ምክንያት ከመኢአድ ፓርቲ የተባረሩትንና በኋላም በህገ ወጥ ማህተም ሲጠቀሙ በመገኘታቸው ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ከሷቸው ከአንድ ዓመት በላይ ታስረው የተፈቱትን ዶ/ር ታዬ ምስ ቦጋለን የመኢአድ መሪ እንደሆኑ አስመስሎ ኢሳት የዜና ሽፋን መስጠቱ ከጋዜጠኝነት ሥነ ምግባር የወጣ ሌላው የጣቢያው አፍራሽ ተግባር ነው።

በሌላም ጊዜ ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲን በሊቀመንበርነት የመሩትና ለእስር እና ለእንግልት የተዳረጉትን ጠንካራ የመኢአድ መሪ የክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልን የጤንነትን ሁኔታ ለመግለጽ ኢሳት ያሰራጨው ዜና እጅግ የተጋነነ ከመሆኑም በተጨማሪ ኢሳት ለመኢአድ ያለውን ጥላቻ በግልጽ ያሳየበት ነበር።

በተለያዩ ጊዜያትም ከአዲስ አበባ ውጭ ያሉ የመኢአድ አባሎች በወያኔ ካድሬዎች ሲታሰሩ ኢሳት የሌላ ፓርቲ አባሎች እንደታሠሩ አድርጎ ሲዘግብ ቆቷል። የመኢአድን ድካምና ልፋት ኢሳት ለሌላ ፓርቲ እንዲቆጠር ለማድረግ ያካሄደው ውጤት አልባ ጥረት ሌላውን ያበረታታ መስሎት ይሆን? ይህ ለኢሳት ብዙ አያራምደውም ምክንያቱም ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ነውና የመኢአድን ብርታትና ጥንካሬ በሃሰት ለሌላ ማስተላለፍ አድማጭን ለጊዜው ሊያደናግር ቢችልም ለዘለቄታው ግን አመኔታን ያሳጣበታልና።

የኢሳት ቴሌቪዥንና ሬድዮ ሥርጭት ኃላፊዎች እነዚህና ሌሎችንም ዘገባዎችና ቃለ መጠይቆችን በሃሰት መረጃዎች አጅባችሁ በማቅረብ በመኢአድ ላይ አፍራሽ ዘመቻ ለማካሄድ የምታደርጉት ሙከራ የህዝብ ጠላት የሆነው ወያኔ ከሚያካሂድብን ፕሮፖጋንዳ የማይለያችሁ መሆኑን ልታውቁት ይገባችኋል። እናንተም የሃሰት ፕሮፖጋንዳ እየነዛችሁ ተቃዋሚን ለማዳከም የምታከናውኑት ተግባር ለወያኔ አገልጋይ ከሆኑት ከኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን የማይተናነስ መሆኑን መረዳት አይቸግርም።

በቅንጅት ጊዜ ቅንጅትን ቅንጅት ያሰኘና ለቅንጅት ፓርቲ ተልዕኮ መሳካት ትልቁን አስተዋጽኦ ያበረከተው የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት መሆኑን እንኳን ወዳጆቻችን በምርጫው በዝረራ የተሸነፉት ተቀናቃኞቻችንም ቢሆኑ የማይክዱት ሃቅ ነው። መኢአድ

ዛሬም ለህዝብ ቆሞ በወኔና በታላቅ ቆራጥነት በመታገል ላይ ይገኛል። ታዲያ ኢሳት ምን ዓላማ ይዞ ቢነሳ ይሆን ለህዝብ ቆሞ መስዋዕትነት እየከፈለ በሚገኘው መኢአድ ላይ አፍራሽ ፕሮፖጋንዳ እየነዛ የሚገኘው?

የሃሰት መረጃ ለህዝብ የሚያቀርብ መገናኛ ብዙኃን የጋዜጠኝነትን ሥነ ምግባር ከመጣሱም በተጨማሪ በህዝብ አመኔታ እያጣ ይመጣል። የኢሳት ጋዜጠኞችም በመኢአድ ላይ እያሰራጫችሁት ያላችሁት የሃሰት ፕሮፖጋንዳ መልሶ እናንተኑ አመኔታ የሚያሳጣችሁ፣ የሚያስንቃችሁና እንድትጠሉ የሚያደርጋችሁ መሆኑን ተገንዝባችሁ እርምት ልትወስዱ ይገባል እንላለን።

ለዲሞክራሲና ለሰብአዊ መብቶች መከበር መስዋዕትነት የሚጠይቀውን የአገር ቤቱን ህዝባዊ ትግል በመሸሽ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ ውጭ የወጣችሁ አንዳንድ ግለሰቦች የኢሳትን ቴሌቪዥንና ሬድዮ መጠቀሚያ በማድረግ በመኢአድ ላይ እያከናወናችሁ ያላችሁት ዘመቻ ከነፃ ፕሬስ መርህ ውጭ በመሆኑ ልትታቀቡ ይገባል እንላለን።

የመኢአድ አባላትና አመራሮች በአሁን ወቅት ከፍተኛ አፈናና እረገጣ በሚፈጸምባት ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነው ለህዝብ መብት መከበር ከወያኔ ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጠው እየታገሉ ያሉ እንጂ እንደናንተ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሚከበሩባት አገር ውስጥ አለመሆናቸውን ልትረዱ ይገባችኋል። በአሁን ወቅት የመኢአድ አመራር ጭንቀታቸው በከፍተኛ ደረጃ እየታየ ያለው የህዝብ መነቃቃትና የሥርዓት ለውጥ መፈለግ በህዝብ ላይ እልቂትና አደጋ ሳይደርስ በብልሃትና በዘዴ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን በሰላማዊ መንገድ የሚሰፍንበትን መንገድ ማመቻቸት ላይ ነው። የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት በትልቅ ደረጃ እያሰበ እያለ እናንተ ግን በሃሰት ፕሮፖጋንዳ እንቅስቃሴዎቹን ልታውኩ መሞከራችሁን ቁብ የማይሰጠው መሆኑን መኢአድ መግለጽ ይወዳል።

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!**

Central Executive Office ALL ETHIOPIA UNITY PARTY AEUP